ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

የካቲት 2003 ዓ.ም. የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ቁጥር 28

# በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወጪ መጋራት

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡

በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም.ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፡፡

በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መስንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

## መግቢያ

ዘመናዊ ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ከመቶ ዓመት በላይ ሲሆን ከፍተኛ ትምህርት ከተጀመረ ከሃምሳ ዓመት በላይ አስቆጥሯል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2009 እንደሚገልፀው ከፍተኛ ትምህርት ማለት በሥነ ጥበብ፤ በማህበራዊ ሳይንስና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች በቅድመ ምረቃና በድህረ ምረቃ የዲግሪ ፕሮግራሞችን በመደበኛ፣ በተከታታይና በርቀት ወይም በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ እየታገዘ የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡

በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ጉዞ በጣም አዝጋሚ ነበር፡፡ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር 1991 ድረስ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቁጥር ሁለት ብቻ ሲሆኑ እ.ኤ.አ. በ2010 ግን 23 ደርሰዋል፡፡ በእነዚህ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ መደበኛ ተማሪ ዎች ቁጥር በ2001 ዓ.ም. ወደ 263,953 ደርሷል፡፡ ይህም ሆኖ ግን ከአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ዕድገት አነስተኛ ነው፡፡ ስለዚህ ሀገራችን ወደፊት በዚህ መስክ ብዙ ሥራ ይጠበቅባታል፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከፍተኛ ትምህርት ብዙ ወጪ የሚጠይቅ ነው፡፡ ለምሳሌ ትምህርት ሚኒስቴርና ዩኔስኮ በጋራ እ.ኤ.አ በ2005/06 ጥናት አካሂደው የአንድ ተማሪ በየደረጃው በነፍስ ወከፍ ወጭው ምን ያህል ነው የሚለውን ለመመለስ ሞክረዋል፡፡ በዚህም መሠ ረት በ1998 ዓ.ም. የአንደኛ ደረጃ (1-8) የነፍስ ወከፍ ወጭው ብር 205 ሲሆን የከፍተኛ ትምህርት ብር 6,646 (ስድስት ሺህ ስድስት መቶ አርባ ስድስት) ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት አገሪቱን ከድህነት ለማውጣት አራት ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን የልማት ዘርፎች ለይቶ አስቀምጧል፡፡ እነዚህም፣

1. መንገድ
2. ትምህርት
3. እርሻና የተፈጥሮ ሀብት
4. የጤና ዘርፍ ናቸው፡፡

ትኩረት ከተሰጠው የትምህርት ጉዳይ ውስጥም አንዱ የከፍተኛ ትምህርትን በማስፋፋት የአገሪቱን የሠለጠነ የሰው ኃይል በብዛት ማም ረት ነው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ዕድልን ለማስፋት ደግሞ ወጨውን በተጠቃሚ ዎች ማስደጎም ያስፈልጋል ብሎ መንግስት ያምናል፡፡ በዚህም መሠረት እ.ኤ.አ. ከ2003/04 ጀምሮ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመደበኛው ፕሮግራም የሚሳተፉ

ተማሪዎች መንግሥት በሚያወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የትምህርት ወጪአቸውን ከመንግሥት ጋር በመጋራት እንዲሸፍኑ ተወስኖ በሥራ ላይ ከዋለ ወደ ስምንት ዓመት ሆኖታል:: ይህ የወጭ መጋራት ሕግ ሆኖ ከፀደቀ በኂላ በርካታ ተመራ ቂዎች የከፍተኛ የትምህርት ተቋም ትምህርታ ቸውን አጠናቀው ወደ ሥራ ዓለም ተሠማርተዋል:: በገቡት ውለታ መሠረትም ያለባቸውን የትምህርት ዕዳ መክፈል ጀምረዋል::

ስለሆነም ወጪ መጋራት በሕግ ፀድቆ ተግባራዊ ከሆነ በኂላ የታየው ተሞክሮ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምን እንደሆኑ ለመዳሰስ በሁለት የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማለትም በአዲስ አበባና በአዳማ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ይህን ጥናት በ2002 ዓ/ም አስጠንቷል::

## 2. የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው:-

ሀ/ በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በወጪ መጋራት የተነሳ ግብዓቶችን በማጠናከርና በመማር/ማስተማር ሂደት ላይ ያደ ረገውን ተፅዕኖ ለመመርመር፣

ለ/ ወጪ መጋራት በሥራ ላይ ከዋለ በኂላ እስከአሁን ምን ትምህርት (ተሞክሮ) እንደተገኘ ለመዳሰስ፣

ሐ/ ከተጠቃሚዎች እስካሁን የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን አገልግሎቱን ለማወቅና በአሰባሰቡ ሂደት እስካሁን የታዩትን ችግሮች ለመቃኘት፣

መ/ የሌሎች አገሮች ልምድ በተለይም የአፍሪካ ምን እንደሚመስል ዳሰሳ ለማድረግ ነው::

## 3. የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች

በጥናቱ ዓላማ ለተነሱ መሠረታዊ ሀሳቦች ምላሽ ለመስጠት በመረጃ መደገፍ ያለባቸው ጥያቄዎች ተነስተዋል:: እነሱም፣

ሀ/ የወጪ መጋራትን ተመን ለመወሰን ምን ዓይነት ዘዴ ተግባራዊ ሆኖ ነበር?

ለ/ የወጪው መጋራት ተመን ሲወሰን የተካፈሉ ባለድርሻ አካላት እነማን ናቸው?

ሐ/ ወጪ መጋራት ምን ያህል በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተግባራዊ ሆኗል?

መ/ የመማር/ማስተማር ግብዓቶችን በማሻሻል ረገድ መምህራን፤ ተማሪዎች የወጪ መጋራትን ጉዳይ እንዴት ያዩታል?

ሠ/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጭ መጋራትን ደንብ ተግባራዊ ሲያደርጉ ያጋጠማቸው እክል ምን ነበር?

ረ/ መንግሥት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በኩል ከተጠቃሚ ተመራቂዎች ዕዳ ለመሰብሰብ የዘረጋው አሠራር ምን ያህል ውጤታማ ነው?

## 4. የጥናቱ ወሰን

በ2003 ዓ.ም. በኢትዮጵያ 23 የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አሉ:: በእነዚህ ተቋማት ወደ 254,192 የሚጠጉ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎችና 11,026 መምህራን ይገኛሉ:: ይህ ጥናት የተካሄደው ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ገቢ ዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ከተመራቂ ተማሪ ዎች፣ በአዲስ አበባና ከአዳማ ዩኒቨርሲቲዎች በተገኙ መረጃዎች ነው:: በመሆኑም ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ሁሉንም የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አያጠቃልልም::

## 5. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ ያተኮረው በናሙናነት በተመረጡት በአዲስ አበባና በአዳማ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ነው:: ጥናቱ በእነዚህ ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ላይ በመመሥረት በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዙሪያ ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች ቃኝቷል::

በጥናቱ የተለያዩ ግለሰቦችና የሚመለከታቸው ክፍሎች ተሳታፊ ሆነዋል:: እነሱም:-

- 565 የአዲስ አበባና 466 የአዳማ ዩኒቨርሲቲ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች፣

- የአዲስ አበባና የአዳማ ዩኒቨርሲቲ የወጪ መጋራት ቢሮ ኃላፊዎች፣
- ከአዲስ አበባና ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ በወጪ መጋራት ሂደት አልፈው የተመረቁ ተማሪዎች፣
- የወጪ መጋራት ጉዳይ ኃላፊ ከትምህርት ሚኒስቴር፣
- የወጪ መጋራት ጉዳይ ኃላፊ ሆነው የሚሠሩ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣
- 59 መምህራን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ እንዲሁም 64 መምህራን ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ ናቸው::

መረጃዎች የተሰበሰቡት የጽሑፍ መጠይቅንና ቃለ መጠይቅን ተግባራዊ በማድረግ ሲሆን ጥናቱን ለማዳበር ወጪ መጋራትን በተመለከተ የመንግሥት አዋጆችን ትምህርት ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ገቢ ዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወጪ መጋራትን ተ ግባራዊ ለማድረግ ያወጡዋቸው የውስጥ ደንቦችና መመሪያዎች በጥንቃቄ ታይተው ጠቃሚ ሀሳቦች በጥናቱ ተካተዋል::

ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በስታቲስቲካዊና በጽሑፍ ገለጻ መንገድ የተተነተኑ ሲሆን ዋና ዋና የጥናቱ ግኝቶችም የሚከተሉት ናቸው::

## 6. ዋና ዋና የጥናቱ ግኝቶች

6.1 እስከ አሁን ድረስ መንግሥት የወጪ መጋራትን በተመለከተ አራት ሕጎችን አውጥቷል:: ከነዚህም ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤ ት ደንብ ቁጥር 154/2008፣ ስለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/2003፣ የግብር ገቢ አዋጅ ቁጥር 286/2002 እና የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 154/2008 ናቸው::

6.2 ወጪን ለመጋራት ውል የፈረሙ ተማሪዎች የመኝታ፣ የምግብና፣ የሕክምና ወጪዎቻ ቸውን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍኑ ሲሆን ለትምህርታቸው ከሚወጣው ወጪ 15% ይሸፍናሉ:: ተመራቂዎች ይህን ዕዳቸውን የሚከፍሉት በተለያየ መንገድ ነው:: በጤናና በትምህርት ዘርፍ የተሰማሩ ተመራቂዎች ለመንግሥት ተቋማት አገልግሎት በመስጠት ዕዳቸውን መክፈል ይችላሉ:: ሌሎች ምሩቃን ሠርተው ከሚያገኙት ገቢ 10% በመክፈል ከአሥራ አምስት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ዕዳቸውን ማጠናቀቅ ይችላሉ:: ሆኖም ከተ መራቂዎች ውስጥ የመክፈል አቅም ያላቸው ከፈለጉ ያለባቸውን ዕዳ በአንድ ጊዜ ወይም በአጭር ጊዜ በመክፈል ከዕዳቸው ነፃ ሊወጡ ይችላሉ::

6.3 መንግሥት የመኝታና የምግብ ተመን የመወሰን ሥልጣን ሲኖረው የከፍተኛ ትምህርት ተቋ ማት ለመማር ማስተማር የሚወጣውን ወጪ (tuition fee) ይወስናሉ:: የወጪ መጋራት ሕግ ከተደነገገ ወዲህ መንግሥት በተማሪዎች የምግብ ዋጋ ተመን ሁለት ጊዜ ለውጥ (ጭማሪ) አድርጓል::

6.4 የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የወጪ መጋራትን አስፈላጊነት ተቀብለውታል:: ሆኖም ግን በመማር/ማስተማር ሂደት ላይ አዎንታዊ ተፅ ዕኖ እንዳላመጣ ገልጸዋል::

6.5 ተማሪዎች የወጪ መጋራትን አስፈላጊነት ቢቀበሉም ከሚማሩበት ተቋም የሚያገኙት አገልግሎት በቂ እንዳልሆነ ለጥናቱ በሰጡት መልስ አረጋግጠዋል::

6.6 ከሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች መጠይቁን ከመለሱት ተማሪዎች 80.3% የመኝታና የምግብ አገልግሎት፣ 4.7% የሚሆኑት ደግሞ የመኝታ አገልግሎት ብቻ የሚያገኙ ሲሆን የመኝታ አገልግሎትን ግን በጥሬ ገንዘብ ይወስዳሉ:: እያንዳንዱ ተማሪ ሲመረቅ በዕዳ መልክ ይዞት

የሚወጣው መጠን እንደሚሰለጥንበት የሙያ መስክ የተለያየ ይሆናል።

6.7 መጠይቁን ከመለሱት ተማሪዎች ውስጥ 75% የሚሆኑ የመጡት ከተማ ውስጥ ከሚገኙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ የቀሩት ከገጠር 2ኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ነው።

6.8 መንግሥት ከተመራቂዎች በኢትዮጵያ ገቢ ዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በኩል የሚሰበስበውን ገንዘብ ወደ መንግሥት ካዝና ያስገባል እንጂ ለመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መልሶ ገቢ አያደርግም። በዚህም ምክንያት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ሕግ ሥራ ላይ ከዋለ ወዲህ በቀጥታ ያገኙት ጥቅም የለም። መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በአብዛኛው ይህን ሁኔታ በሰጡት መልስ አንፀባርቀዋል።

6.9 ማንኛውም ተማሪ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚማር ከሆነ ወጪን ለመጋራት ውል መፈረም አለበት። የዚህ ዓይነት አሠራር በብዙ አፍሪካ አገሮች የተለመደ አይደለም።

6.10 ዕዳቸውን መክፈል የጀመሩ ተመራቂዎች እንደሚሉት ከገቢያቸው 10% መክፈል በኑሮአቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮባቸዋል። ይህ የክፍያ መጠን ከሌሎች ሀገሮች ልምድ አንፃር ሲታይም ከፍተኛ ነው።

6.11 በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለው የሥራ ግንኙነት እንደተፈለገው ጠንካራ አይደለም። በመሆኑም የሥራ ክፍተቶች በጥናቱ ጊዜ ታይተዋል።

6.12 ከብዙ አፍሪካ አገሮች ተሞክሮ እንደታየው ከተመራቂዎች የወጪ መጋራት ዕዳ መሰብሰብ እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው አስተማማኝና ቀልጣፋ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ካልተዘረጋ ሁኔታው አስቸጋሪ ይሆናል።

## 7. የመፍትሔ ሀሳቦች

በጥናቱ በተሰበሰበው መረጃ ላይ በመመሥረት የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች ተሠንዝረዋል።

7.1 በሌሎች ሀገሮች እንደሚደረገው ሁሉ ከወጪ መጋራት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለዩኒቨርሲቲዎች ወጪ መሸፈኛ እንዲውል ቢደረግ፣

7.2 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት ክፍያን ለመሰብሰብ በቂ የሰው ኃይልና ግብአቶች ስለሌለው ይህ ቢሻሻል፣

7.3 ከከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚዎች ከወር ገቢያቸው የሚሰበሰበው 10% በኢትዮጵያ የኑሮ ደረጃ ከፍተኛ በመሆኑ የክፍያው መጠን ኑሮአቸውን ባገናዘበ መልኩ ቢሆን ይመረጣል።

**ዋና ሌቃ (ዶ/ር)**
**ደሳለኝ ጫልችሳ (አቶ)**

**ምንጭ**፡- Wanna Leka and Desalegn Chalchisa. 2010. "*Cost sharing in public higher education institutions in Ethiopia,*'' a study commissioned by Forum for Social Studies (FSS), Addis Ababa.

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሰነድ የታተመው በለጋሾች ቡድን የገንዘብ ድጋፍ ነው። ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲያኑ ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሾች ቡድንን ወይም የአሳታሚውን አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም።

አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
❄ ስልክ 011-629 78 88/91 ❄ ፋክስ 011-629 78 89
❄ ኢሜይል: fss@ethionet.et ❄ ድረ-ገፅ www.fssethiopia.org.et